**የመካከለኛው ምስራቅ የሉኣላዊነት የሀይማኖትና የዉሀ ዋስትና ችግሮች:**

**ለኢትዮጵያ ከባድ ስጋት፤**

**በያረጋል ይማም.**

*ይህ ጽሁፍ ረጅም ሊሆን ይችላል፤ መቆራረጥ ወይም በሁለት ግዜ ማውጣት ሃሳቡን ይበታትነዋል ከሚል ባንዴ አዉጥቸዋለሁ፤ አገራችን ያለባትን የዉጭና የውስጥ በታኝ ችግሮች እንድንረዳና ትግላችን አቅጣጫ እንድናስተካክል ትንሽም ቢሆን መረጃ ሊሆናን ይችላል፤*

*ጽሁፉ በአፍሪካ ቀንድ ላይ ያንዣበበዉን የእከክልኝ ልከክልሀ ከባድ ጦርነት ለኢትዮጵያ እጅግ አደገኛ የሉዋላዊነት ፈተና የሆነዉን ይዳሣል፤ በዚህ የጦርነት ከበሮ ድለቃ እነማን እንደተሰለፉ ማን ከማን እንደሚተባበሩ ሊተባበሩበት የቻሉበት ምክንያቶችና የእየአገሮች ችግሮች የችግሮችን ምንጭና አመጣጥ በመጠኑ ይዳሣል፤ አገራችን ኢትዮጵያን በምን እንደሚያሰጋት ይዳሣል፤ በዋናነት ሳዉዲ አራብያ ቱርክ ኢራንና ግብጽ ለዚህ ያንዣበበ ጦርነት ዋና ተዋናኝ ያደረጋቸዉን ምክንያት ይዳሣል፤ ለዉክልና ጦርነትና (proxy war) ፊት ለፊት እነማን እንደተመረጡ ማን ከማን ጋር በምን ምክንያትስ እንደወገነ ያብራራል፤*

**በቱርክና ኢራን ላይ ያንዣበበዉ የሉዋላዊነት አደጋና ይህን ለመከላከል የሚከተሉት ስልት፤**

በ 1919 አንደኛው የአለም ጦርነት ሲያከትም የኦቶማንን የ500 አመት ግዛት አክትሞ ተራውን ለአዉሮፓዉያን በተለይ ለእንግሊዝና ፈረንሳይ አስረክቦ ተደመደመ. አሁን መካከለኛው ምስራቅ እያልን የምንጠራው ወደ 500 አመታት በኦቶማን ቱርክ ሱልጣን ግዛት ስር ነበር፣ በ አንደኛው አለም ጦርነት ማክተም ጀምሮ በአካባቢው ብዙ አገሮች ነጻነታቸዉን እያገኙ መፈጠር ጀመሩ. ኢራን ሶርያ ኢራቅ ሊባኖን ሳውዲ አራቢያ እንዲሁም ሊሎች. ከ1922 ከመጀመሪያዋ ግብጽ ነጻነት በፊት ግን አንድም በነጻነት የሚተዳደር የአረብ አገር አልነበረም.

አንደኛው የአለም ጦርነት ማክተምን ተከትሎ አለም በአዲስ ገዥወች ተቀይሳ እንደ አዲስ ስትዋቀር እነ ኢራን ሶሪያ ኢራቅና ቱርክ የሚባሉ አገሮች ተፈጥረው ድንበራቸውን ሲያካልሉ ኩርድ የተባሉ ዘሮች (አረብ ያልሆኑ ሱኒ ሙስሊሞች) በወቅቱ በአካባቢው የነበረውን አለመረጋጋትና ጦርነት ተጠቅመው አገር ለመመስረት ሞክረው ነበር፤ ኦቶማን ቱርክን ገርስሠው አካባቢዉን የተቆጣጠሩትን ከእንግሊዝና ፈረንሳይ ጋር በሚያደርጉት የፍቀዱልንና እርዱን ድርድር ተስፋ አግኝተው የነበር ቢሆንም ችግሩ ግን እራሳቸው ኩርዶች በዉስጣቸው እርስበርስ መተባበር እንድነትና ቁርጠኝነት መጉደል ትልቅ እንቅፋት ሆኖባቸው ነበር፤ የተወሰኑት ኩርዶች ከቱርክ መንግስት ጋር በማበር ለነጻነት የተነሱትን ወገናቸዉን ይቃወሙ ነበር። በወቅቱ የነበረው የቱርክ መንግስት ኩርዶችን እና አርመኖችን ይህን የነጻነትና የብሄርተኝነት እንቅስቃሴ በመቃወም ከበድ ያለ እርምጃ ወሰደባቸው። በዛም ላይ የእንግሊዞች ለኩርዶች አገር እንዲመሰርቱ ቃል ከገቡ በኋላ እንግሊዞች የተለመደ የፖለቲካ ባህሪ ተጨምሮበት ኩርዶች እስካሁን አገር አልባ እንዲሆኑ አደረጋቸው፤ መጨረሻ ኩርዶች አገር ሊያካልሉ ሲሉ ቱርክ ኢራቅ ሶሪያ እና ኢራን መሬታቸዉን ተቀራምተው ወስደዉት ስለነበር ምንም ማድረግ ሳይችሉ ቀሩ፣ አንድ የነበሩት ኩርድ በአራት አገራት ስር ተከፍለው መተዳደር

ተጀመሩ። ከ 1880 ዎቹ ጀምሮ በተናጠል የግዛት ጥያቄ አመጽ ሲያደርጉ የቆዩት በቱርክ የተጠቃለሉት ኩርዶች ከኢራቅ ኩርዶች ጋር በመተባበር በ አብደላ ኦቻላ የሚመራ PKK (Kurdish Workers Part) የተባለ የአማጺ ድርጅት በ1978 አካባቢ መስርተው በዘመናዊነት አደራጅተው አገራቸውን ነጻ ለማዉጣት በተለይ ከቱርክና ኢራቅ ጋር በትጥቅ መፋለም ጀመሩ፤ የ PKK አማጽያን ቡድን የኩርድ የነጻነት ጥያቄና የትጥቅ ትግል አንግቦ መነሳት እነዚህን አራት አገሮች በኩርዶች ላይ ተመሳሳይ አቋም እንዲይዙና ሳይወዱ በግድ ተቻችለው እንዲተባበሩ አደረጋቸው:: ኩርዶች በአራቱም አገሮች ስለሚኖሩ ላንዱም ቢሆን የመገንጠል እድል እንዳይፈቅዱ በጋራ ያዳክሙት ነበር፤፡ የPKK መሪ አብደላ ኦቻላን ልክ እንደ አንዳርጋቸው ጽጌ በተመሳሳይ ሁኔታ በ 1999 በ CIA ጠቋሚነት በስራ ጉዞ ላይ እያለ የኬንያ ፖሊስ ከናይሮቢ ኬንያ አፍኖ ለቱርክ ተላልፎ ከተሰጠ በሁዋላ የኩርዶች PKK የነጻነት ትግል እየተዳከመ መጣ፤ በወቅቱ ናቶ ቱርክን እሽሩሩ ይላት ሰለነበር ነገሩን ምእራባዉያን ችልታን ነበር የመረጡት.

*(ልብ በሉ ኩርዶች ያለፈቃዳቸው ነው ከአራት የተከፈሉት፣ አንድ አይነት የሚናገሩ አንድ አይነት ዘር እና ሀይማኖት ነው ያላቸው፣ እዚህ ላይ የኛን አፋር ህዝቦች አስቧቸው፣ ድሮ አንድ ነበሩ፣ መጀመሪያ የጂቡቲና የኢትዮጵያ አፋር መባል ጀመሩ፤ ወያኔና ሻቢያ ሲመጡ ያለፈቃዳቸው እንደገና ወደሰስት ተከፈሉ፤ አንድ አይነት አፋሮች ያለፈቃዳቸዉና ያለ ታሪካዊ መነሻ ከ ሶስት ተከፈሉ፤ ይህ ዉሎ አድሮ ምን ያመጣ ይሆን?)*

*ወያኔም አማራዉን እንደ ኩርዶች ለማድረግ ነው እየሰራ ያለው፤ ወልቃይት ጸገዴን ራያን ወስዷል፣ ቤንሻንጉል ብሎ መተከልን ከጎጃም ወስዷል፣ ለሱዳንም በቋራና መተማ መሬት ሰጥቷል እየሰጠም ነው፣ ወደፊት አማራዉን ከኦሮሞጋር በግዛት የማያባራ ጥል ውስጥ ለመክተትም እየሰራ ነው፤ መሀል ወሎ ላይ ኦሮሚያ ዞንበሚል ባቲ ትጠራለች፡ ኢትዮጵያን ካፈረሳት አማራው ግዛቱን ለማስመለስ ለማስተካከል መዋጋቱ አይቀርም፣ ታላቋ ትግራይ ሱዳን መጪዋ ኦሮሚያ እና ሌሎችም በአማራው ላይ ይተባበራሉ። ምክንያቱም ሁሉም ከአማራው ግዛት ወስደዋል፤*

ዘመን ሲቀያየር ነገሮች ይቀያየራሉና ምእራባዉያን በቡሽ የችኩልነት ዘመቻ በ2001 ኢራቅን ወረው ሳዳም ሁሴንን ከስልጣን አስወግደው ጠንካራና ግዙፉን የኢራቅ ጦር ሲበትኑት የአካባቢው ሁኔታ መቀያየር ጀመረ፤ ተዳክመው የነበሩትና በአራት አገራት ተከፋፍለው ለነበሩ ኩርዶች ከ 100 አበት በሁዋላ ሌላ አዲስ ተስፋ ብቅ አለ፤ የኢራቅ ኩርዶች የባግዳድ ማእከላዊ መንግስት መዳከሙን እድል ተጠቅመው በ አሜሪካኖችም እርዳታ የራስ ገዝ አስተዳደር መስርተው በኢራቅ ማእከላዊ መንግስት ስር እዲኖሩ አደረጋቸው፤ በዚህም ላይ ክፍለሀገራቸው ከፍተኛ ነዳጅ ስላላቸው ብዙ ቢሊዮን ዶላር ድርሻቸዉን ስለሚያገኙ ወታደራዊ ደህንነትና ዲፕሎማሲያዊ መዋቅራቸውን ሲያጠነክሩ ቆዩ፤ ታዲያ ባለፉት 5 አመታት ባልታሰበ ISISI በተባለ ሽብርተኛ አማጺ ቡድን ዘመቻ አካባቢው ሲወረርና የኢራቅ ማእከላዊ መንግስት ሲዳከም የኢራቅ ኩርዶች እድሉን በመጠቀም September 2017 የመገንጠል ህዝበ ዉሳኔ ሲያደርጉ 93% መገንጠሉን ደገፉ፣ ይህ ተግባር በከፍተኛ ሁሜታ ቱርክንና ኢራንን አስደንግጦ የቱርኩ መሪ ወደኢራን አቅንቶ ዉይይት አደረጉ፣ ደካማዉን የባግዳድ የሺአ መንግስትም ጠንከር እንዲል ለኩርዶች የመገንጠል እድል ቀዳዳ እንዳይከፍት በማንኛዉም ነገር ከጎኑም እንደሚቆሙ ቱርክና ኢራን አበረታቱት፤ ምክንያቱም የኢራቅ ኩርዶች ተገነጠሉ ማለት ነገ በቱርክ በኢራንና ሶርያ ስር ያሉ ኩርዶችን የትግል

ሞራላቸው ተነሳስቶ ለቱርክ ኢራንና ሶርያ ትልቅ የሉዋላዊነት ፈተና ይሆናሉ ተብሎ ስለታሰበ ነው፤ በዚህም ላይ በነዳጅ ሀብት የታደለው ከኢራቅ የሚገነጠለው አዲሱ ኩርዲስታንም በስዉርም ይሁን በግልጽ ይረዳቸዋልም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው.

ይህ ሁኔታ ለቱርክና ኢራን የጋራ የሉአላዊነት ችግር ስለሆነባቸው የኢራቅ ኩርዲስታንና ህዝበዉሳኔዉንና አጠቃላይ የኩርድን ፖለቲካ  በጋራ ለመቀልበስና ይህን ይደግፋሉ ብለዉ የሚታሰቡ የዉጭ ሀይሎችን በጋራ በዲፕሎማሲም ሆነ በወታደራዊ በተገኘው መንገድ በመፋለም ሉዋላዊነታቸዉን ለመጠበቅ ግልጽና ከፍተኛ ዘመቻ ከፍተዋል፤ ስራቸዉንም የጀመሩት የመካከለኛውን ምስራቅ ፖለቲካ ለመቆጣጠር ከፍተኛ ዘመቻ ከፍተዋል፤ ይህን አላማቸዉን የሚጋራ የሚደግፍ አገር እንኳ ቢያጡ ጥቅም ፈላጊ ደካማ አገሮችን እየፈለጉ አጋር ለማድረግ ሩጫ ይዘዋል፤ ለዚህም አንዱ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች ተመራጭ ሆነዋል፤

## ሳዉዲ አራቢያና ኢራን ጥል መነሻው ምንድነው?፤ ዘመቻቸው  የሀይማኖት የበላይነትን ለማስጠበቅ ነው።

እስልምና ሲነሳ ሳዉዲ አራቢያን ማያያዝ የተለመደ ነው፣ የአለማችን ሙስሊም አብዛኛው የሱኒ ሙስሊም ሲሆን በጣም ትቂቱ ደግሞ የሺአ ሙስሊም ተከታይ ነው፤ ሱኒ ሺአ የሚል ልዩነታቸው የተጀመረው ገና ከጅምሩ ነብዩ መሀመድ (ሰዐወ) እንዳረፉ እሳቸዉን የሚተካ የሙስሊሙ ካሊፍ ማን ይሁን ሲባል ነው፤ ከፊሉ ከሳቸው ቤተሰብ የሆነ ይሁን ሲል ከፊሉ ደሞ ከየትም ይሁን ግን በምርጫ ይሁን ተባለ፤ ከሳቸው ቤተሰብ ይሁን የሚሉት አሊ ይሁን አሉ፤ ምክንያታቸዉም የእሳቸው የነብዩ ሞሀመድ (ሰዐወ) የልጅ ባል ስለሆነ ( የፋጡማ) ከሳቸው ጋር እብሮ ስለቆየ የሳቸዉን ብዙ ነገሮች ሊያውቅ ስለሚችል እሱ ይሁን አሉ፣ የሆነው ሆኖ አቡበከር የነብዩ ተተኪ ሂኖ ተመረጠ፤ አቡበከር ሲያርፍ ሁለተኛዉ ላይም በክርክር ኡመር ቢን-አልካቲብ ያዘ፤ ሶስተኛውላይም ኦኡስማን ቢን-አፋን ሆነ፣ ቀጥሎም አሊ ኢብን -አቡ-ታሊብ አራተኛው ሆኖ ተመረጠ፤ **(የነብዩ ሙሀመድ የልጅ ባል)** በዚህን ግዜ (ሺአት አሊ) ደጋፊዎች ከነብዩ ሞሀመድ ቀጥሎ ሁለተኛው ካሊፍ ነው ለማለት ሞክረው ነበር፣ ምክንያቱም ሶስቱ ተመርጠው ሳይሆን በተጽኖ በትንሽ ሰወች ድጋፍ ነው በታዉን የያዙት የሚል መከራከሪያ ያሰሙ ነበር፤ ከዚህን ግዜ ጀምሮ ነው ሺአት አሊ (የአሊ ቡድን) የሚል ስያሜ የጀመረው. ስለዚህ ሺአ ማለት ቡድን ማለት ነዉ፤ ሌላ ትርጉም የለዉም።

እየቆየ ሲሄድ ቡድናቸው ለይቶለት ልዩነታቸው እየሰፋ ሄዶ ተራርቀው መኖር ጀመሩ፤ አልፎ አልፎ እነዚህ ቡድኖች ወደ ግጭትና ጦርነት ይገቡ ነበር፤ ከብዙ አመታት በኋላ የአሊ ልጅ ሁሴን የነብዩ ሞሀመድ (ሰዐወ) የልጅ ልጅ (የፋጡማ ልጅ ከ አሊ የተወለደ) የሺአዎች መንፈሳዊ መሪ ሆኖ ኢራቅ ካርባላ ይኖር ነበር፤ እንደተለመደው በሱኒ ደጋፊዎችና ሺአዎች መካከል ጦርነት ሲካሄድ ሱኒ ተዋጊዎች በርትተው ካርባላን ለመቆጣጠር ተቃረቡ፣ ሁሴን ህዝብ እንዳያልቅ በሽምግልና ለመፍታት ሞክሮ የነበረ ቢሆንም፤ ነገር ግን የሺአ ሽማግሌዎች አይሆንም እንደፈሪ ሊቆጠርብን ይችላል ብለው በሙሉ ጦርነት ገቡ፤ ሁሴንም ግንባር ገብቶ ሲያዋጋና ሲዋጋ መስዋት ሆነ፣ ይህች ቀን የሁሴን አሊ በሱኒ መገደል ለሺአ ተከታዮች ትልቅና ዘላለማዊ ሀዘን ሆነባቸው፣ በሱኒና በሺአ መካከል የማይታረቁበት ጥል ውስጥ የከተታቸው ሆነ፤ ሺአዎች

የመንፈሳዊ መሪ ካሊፋቸው አድርገው የሚቆጥሩት የነብዩ ሞሀመድ (ሰዐወ) የልጅ ልጅ ሲገደልባቸው ከባድ መሪር ሀዘን ተሰማቸው፤ እስካሁንም በየአመቱ ካርባላ ከተማ ትልቅ ዝክረ ሞት(የሰማእታት ቀን) እራስን በስለትና በተለያዩ መሳሪያዎች አካልን በመቁርጥና በመጉዳት በሀዘን ይከበራል፤ የሺአ ሀይማኖት ተከታይ ኢራን 97% ይገመታል ሊባኖን ሂዝብ-አላህ (የአላህ ድርጅት) ባህሬን 70% እንዲሁም በትቂት እገሮች በጣም ትቂት ሺአዎች ይኖራሉ፤ ለነዚህ በአለም ላይ ላሉ ሺአ ሙስሊሞች የበላይ ጠባቂ ኢራን ናት፤ በጋዝ ሀብቷ እነዚህ ሺአዎች እንዲጠነክሩ እገዛ ታደርጋለች፣ የሱኒ የበላይ ጠባቂ የሆነችዉን ሳዉዲ አራቢያን ለማዳከም ከፍተኛ ስራ ትሰራለች.

**ዋሀቢዝም እና ሳዉዲ አራቢያ.**

ብዙ ግዜ ዋሃቢዝ ሲባል ከአክራሪነትና ሽብርተኝነት አያይዘው የሚያዩ ብዙዎች ናቸው፣ ዋሃቢ ማለት የ አብዱልዋሀብ ተከታይ ማለት ነው፤ ማርክሲዝም ሌኒንዝም እንደምንለው ነው፤፡ ሞሀመድ አብዱልዋሃብ የሚባል ነጅድ በምትባል የጎሳ ግዛት ባሁንዋ ሳውዲ አራቢያ ሪያድ አካባቢ ነዋሪ ነበር፣ ከነቤተሰቡና ከአካባቢዉ በተለየ መልኩ የእስልምና ሀይማኖት እየተዳከመ ስለሆነ የቁርአንን ህግጋት በትክክል መተርጎም አለብን፤ ባህላዊ እስልምናን (traditional Islam) መከተል አለብን፤ ማለት የሸረእያን ህግ በትክክል ስራ ላይ ማዋል እለብን፤ የሰረቀ እጁ መቆረጥ አለበት ዝሙት የፈጸመ መወገር አለበት እያለ ያስተምር ጀመር፤ ቤተሰቡም ሆኑ ጎሳው ይህን ትምህርቱን አልቀበለው ይላሉ፤ የጎሳው መሪ አብዱልዋሃብን ህዝብን እየጎዳህ ነው ብሎ ይበሱኑ አካባቢዉን ለቆ እንዲወጣ ያባርረዋል፤ ልጆቹንና ሚስቱን ይዞ በደማሽቆና በባግዳድ እየዞረ ቢሰብክ ሰሚ አጣ፤ ዞሮዞሮ ዲራያ ወደምትባል የጎሳ ግዛት (ባሁኑ ሰአት በሳዉዲ ግዛት አካል የሆነች) ሄዶ ይሰብካል፤ የዲራያ ጎሳ ገዢ መሃመድ ቢን-ሳኡድ ይባላል፣ **(የአሁኑ የሳዉዲ ንጉሳውያን ጎሳ)** ትምህርቱ ይመስጠዉና ያስጠጋዋል፤ አካባቢውንና ግዛቱን እንዲያስተምር ይፈቅድለታል፤ የቢን-ሳኡድን ሰራዊትን እየሰበከ ካካባቢው የጎሳ ግዛቶች ጋር በሚደረግ ጦርነት ጂሀድ ጦርነት እንደሆነ በአላህ ስም እያዘመተና መስዋት የሆነ ገነት እንደሚገባ ሲሰብክ የቢን-ሳኡድ ጦር ድል በድል እየሆነ ግዛቱን አስፋፋ’ በዚህን ግዜ አብዱልዋሃብን በጣም ስለወደደዉ የእሱ ብቻ ማድረግ ፈለገ፤ ቢን-ሳዉድ የአብዱልዋሃብን ልጅ በማግባት በትዳርና በማህላ ተሳሰሩ፤ አብዱልዋሃብ ለሌላ የጎሳ መሪ ሄዶ እንዳያስተምር በማህላ ተሳሰሩ፤ የቢን-ሳኡድ ጎሳ አካባቢዉን በጅሀድ ጦርነት የአካባቢዉን ጎሳዎች እየጨፈለቀ ግዛቱን አስፋፋ፤ አካባቢዉ ታመሰ ሀይለኛና ተዋጊ ጎሳ ሆነ ቆየ፤ ይባስ ብሎ በ1802-1803 ወደ ባግዳድና ካርባላ በመዝመት ብዙ ሺህ ሺአዎችን በመደምሰስና በመግደል ብዙ ህጻናትን በምርኮ ይዞ መጣ፤ በዚያን ግዜ መካከለኛው ሳዉዲ ሪያድና እነ መካ አካባቢ ኦቶማን ቱርክ ሰራዊት ብዙ አልነበረም፣ አካባቢው ዉሀ አጠርና ከባድ በረሀማ ስለነበር በቋሚነት የሚኖር መስተዳድር አልነበረም፣ ባግዳድ ደማስቆና እየሩስ አለም የሚኖረው የኦቶማን አስተዳደር በእርቀት ነበር ይህን የሳዉዲን አካባቢ የሚቆጣጠረው።

ይህ የአብዱል ዋሀብና የ ቢን-ሳዉድ ጦርነት እስታንቡል ላለው የኦቶማን ሱልጣን ይደርሳል፤ ግዛቴን የሚያምስ አንድ ሰው ተነስቷል ባስቸኳይ ካላስቆማችሁ የሚል ትዛዝ ሲሰጥ፣ ኢብራሂም አሊ ባሻ የሚባል ካይሮ የሚኖር የኦቶማን ጦር አዛዥ በ 1803 የኦቶማንን ጦር መርቶ ገስግሶ ዲራያ ያሁኑ (ሪያድ አካባቢ)

ይደርሳል፤ የአብዱልዋሀብንና የኢብን-ሳዉድን ሰራዊትና ጎሳ ደምሥሶ ያጠፋል፣ የተፈናቀሉትን ሌሎች ጎሳዎችን ወደነበሩበት ይመልስና አካባቢዉን አረጋግቶ ይመለሳል፤ በአካባቢዉም እንደገና ሰላም ሰፈነ፤

ከአንደኛው አለም ጦርነት ቀደም ብሎ አዉሮፓውያን መካከለኛው ምስራቅን አተኩረውበት ነበር፤ በተለይ እንግሊዝና ፈረንሳይ አገር አሳሽ ሰላዮች እየላኩ ያስጠኑ ነበር፤ የጎሳ መሪና ከኦቶማን ጋር ቅሬታ አላቸው የሚሏቸውን ጎሳዎችና የጎሳ መሪዎች እየቀረቡ በመደለል የነሱ ደጋፊ አድርገዋል፤ የሶስቱ ታላላቅ ሀይማኖቶች መነሻ የሆነ (ጁዲዝም፤ ክርስትና፣ እስልምና) ይህ አካባቢ በኦቶማን ስር ለ 500 አመታት በሰላምና በመቻቻል ይተዳደር ነበር፤ 1ኛው አለም ጦርነት ሲቋጭ የእንግሊዝ መንግስትና ጦር አካባቢዉን ሲቆጣጠር ሂጃዝ በምትባለው ግዛት የአሁንዋ መካና መዲና ጅዳን ጨምሮ ሀሽማይት የሚባል ጎሳ ነበር፤ ጎሳውና መሪያቸዉም የተከበረና በአካባቢዉ የታላቅነት ስሜት የሚሰማው ነበር፤ እንግሊዞች አካባቢዉን ለመቆጣጠር ከኦቶማን ጋር ሲዋጉ ይህ ጎሳ ለእንግሊዞች ትልቅ እገዛ አድርጎላቸዋል፤ ኦቶማን ከተባረረ አገር እንደሚመሰርቱ እንግሊዞች ቃል ገብተዉለት ስለነበር Kingdom of Helaz ብለው መንግስት መሰረቱ፤ ይህ የሀሽማይት ጎሳ ሰፊና በጣም ስልጡን ጎሳዉም እስከ የአሁንዋ ጆርዳንና ኢራቅ የተንሰራፋ ስለሆነ እንግሊዞች ፈርተውት ሳይሆን አልቀረም የከፋፍለህ ግዛው ስልት በመጠቀም ሀሽማይት ጎሳ መሪን ከድተው በድብቅ ለተቀናቃኙና አናሳው **የቢን-ሳኡድ** ጎሳን ማስታጠቅ ጀመሩ፤ በእንግሊዝ ቡራኬና ድጋፍ የዋሃቢዝም አስተሳሰብ ተጨምሮበት **የቢን-ሳኡድ** ጎሳ ከሪያድ ተነስቶ በካባቢያቸዉን ይኖሩ የነበሩትን ሌሎች የጎሳ ግዛቶችን በመጨፍጨፍና ከሪያድ እስከ መካና መዲና ጅዳ በመምጣት የሀሽማይት ጎሳን በመሸፍጨፍ ግዛታቸዉን አስፋፍተው አሁን ሳዉዲ የተባለችዉን አገር መሰረቱ፤ የሀሽማይት መሪዎችንም በግፍ ጨፈጨፏቸው የአዲቷ አገር ሳዉዲ አራቢያ መተዳደሪያና መመሪያም ሸረእያ ሆነ፤ የዋሀቢዝም አስተሳሰብ እንደገና ከ200 አመት በሁዋላ ስራ ላይ ዋለ፤ **የአብዱልዋሃብ እና የቢን-ሳኡድ** ዘሮች እንደገና ንጉሳዊ ቤተሰቦችና የሳዉዲ ገዥ ሆኑ፤ የአገሪቱን ስልጣንና የሀብቷ ፈላጭ ቆራጭ መሪዎች ሆኑ፤ አንዱ ሲሞት ለወንድሙ ወይም ለልጁ እያስተላለፈ ስልጣኑ ከ አብዱልዋሃብ እና ቢንሳኡድ ዘር እንዳይወጣ ትልቅ አጥር ሆናቸው፤ እስካሁንም ገትረው ይዘዋል፤

ልብ በሉ አሁን የሳዉዲ ንጉሳዊ ቤተሰብ ገዢ ቡድን የ ቢን-ሳኡድ ጎሳ ከአብዱልዋሃብ ጋር የተቀላቀለ በአብዱልዋሃብ ዋሃቢስት) አስተሳሰብ የሚመራ አንድ ጎሳ ነው፤ ሳዉዲ ዉስጥ ዋሃቢዝም ወይም ሸረእያ ጠፋ ወይም ተሻረ ማለት የቢን-ሳኡድ ጎሳ አባላት ስልጣናቸውን ያጣሉ፤ ብዙ ቂም ያላቸው የተጨፈጨፉ ጎሳዎችም ይበቀሉናል ብለዉም ይሰጋሉ፤ በተለይ የሀሽማይት ጎሳ አድፍጦ ነው ያለው፣ አንድቀን ስልጣናችን እናስመልሳለን እያሉ በምስጢርም ይዝታሉ።

*(እዚህ ላይ ህወሀትን እያሰባችሁ፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲ እና ኢሃዴግ የለም ማለት የትግራይ ጥቅምና የበላይነት እንደሚያከትም የታወቀ ነው፤)*

ስለዚህ ሳዉዲ አራቢያ ይህን የዋሃቢ አስተሳሰብ ለማስጠበቅ ማንኛዉንም ነገር የፈጀዉን ገንዘብና ሀይል አዉጥታ ትከላከላለች ታስጠብቃለች፤ በነዳጅ ገንዘቧ በመደለል ብዙ አገራትን ከጎኗ ታሰልፋለች፤ በተለይ ተቀናቃኝ የሺአ የበላይ የሆነችዉን ኢራን በጦር መሳሪያ በወታደራዊ ሀይልና በልምድም ከሳዉዲ

ስለምትበልጥ እሷን ለመቋቋም ሌላ የሱኒ አገሮችን ከማስተባበር አልፋ የእስልምና የጋራ ጠላት ከሚሏት እስራኤል ጋር እስከመተባበር ደርሳለች፤ በተለይ ባለፉት ሁለት አመታት የኦባማ አስተዳደር በኢራን ላይ ያሳየዉን ለዘብተኝነት ተከትሎ ሳዉዲ ከ20 በላይ የአካባቢዉና የሌሎች የሚከተሏትን የሱኒ እስልምና ሀይማኖት ተከታይ አገሮችን የጦር ሀይል እስከማስተባበር ደርሳለች፤ ግብጽ በተለይ ዋና የሳዉዲ መመኪያ ናት፤

*የሳዉዲ መንግስትና አንዳንድ ግለሰቦች የተለመደ የዉስጥ አስተሳሰብና አባባል አላቸው "የግብጽ ጦር ጠንካራ ሀይል ነው፤ ይህ ጠንካራ ወታደራዊ ሀይል የግብጽ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሱኒ ሙስሊምና የአረቦች ጦር እንደሆነ ያስባሉ ይመኛሉ፤ ለዚህም ልንንከባከበው ይገባል ይላሉ" ሌላው፤ የፓኪስታን ኑክሊየር የጦር መሳሪያ ብቸኛው የሙስሊም ኒኩሊየር ስለሆነ ሁሉም የሙስሊም አገር ሊንከባከበው ይገባል የሚል ዉስጣዊ አስተሳሰብና አባባል አላቸው"*

**የግብጽ የውሀ ዋስትና.**

የግብጽን ነገር ሁላችንም በተቀራረበ ሁኔታ እንገነዘበዋለን፤ እጅግ በከፍተኛ በረሃማዋ ግብጽ የሚኖረው 90 ሚሊዮን የግብጽ ህዝብ ሙሉ በሙሉ የሚጠጣው የሚመገበው የሚታጠበው እርሻ የሚያመርተው በአባይ ዉሀ ነው፤ አባይ ማለት ህይወት ነው፤ ግብጽ ማለት አባይ ነው፤ ከድሮ ጀምሮ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያ እንዳትረጋጋና እንዳታድግ ስታደርግ ቆይታለች፤ ወያኔ ስልጣን ሲይዝ እነመለስ አባይን እንደማይገድብ ለድሮው የግብጽ ፕሬሲደንት ሙባረክ ቃል ገብተው ነበር ይባላል፤ እንዲያዉም ወያኔ ኢትዮጵያን ሊያፈራርሳት እንደሚችል ሙባረክ ተስፋና ግምት ነበራቸው፤ በዚህም የተነሳ የሙባረክ መንግስትና ባለስልጣናት የአባይ ተፋሰስ አገራት በተለይ ኢትዮጵያ የማያባራ የውስጥ ፖለቲካ ስላለባቸው አባይን የሚቀንስ ትልቅ የልማት ስራ ይሰራሉ ብሎ አላሰበም ነበር፤ የሙባረክ አገዛዝ የወያኔን አላማና ባህሪ በደንብ ያዉቃሉ፤ ኢትዮጵያን በዘር ከፋፍለው መግዛት እንደሚፈልጉ ያዉቃል፤ ይህን የአናሳ የበላይነት አገዛዝ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደማይቀበለውና ሁሌም ያለመረጋጋት እንደሚኖር ያዉቃሉ፤ አንድ ቀን የኢትዮጵያ ህዝብ በአመጽ ወያኔን እንደሚያናጋው ይገነዘቡ ነበር፤ ወያኔም የማይቋቋመዉ ህዝባዊ አመጽ ከመጣበት ታላቋ ትግራይን ገንጥሎ ኢትዮጵያን በትኖ እንደሚሄድ ያዉቁ ነበር ብዬ እገምታለሁ፤ በዚህ ግንዝቤያቸው የሙባረክ ግብጽ በአባይ ተፋሰስ አገራት ሁሌም ቀዉስ ዉስጥ ስለሚሆኑ አባይን የሚቀንስ የልማት ስራ አይሰሩም ብለው ተዘናጉ፤ ላለፉት 20 አመታት አፍሪካን በተለይ የ አባይ ተፋሰስን አገራትን እንደድሮው በትኩረት መከታተል ትታ ያላትን የዲፕሎማሲ ግንኙነትና ስራዎች በብዛት ቀንሳ አካባቢዉን ችላ ብለው ነበር፤

**አዲስና ያልታሰበ የግብጽ ስትራቴጂ፤ ከቱርክ ካታርና ኢራን ጋር ልዩነት፤**

**የግብጽ ህዝባዊ አመጽ፤ የእስላም ወንድማማቾች** (Islam Brothershood) **እና ጄነራል አብደል ፈታህ አል ሲሲ**(CICI)

የግብጹ ኢስላም ወንድማማቾች የፖለቲካ ድርጅት ከ80 አመት በላይ ያስቆጠረ እድሜ ጠገብ ድርጅት ከመሆኑ በላይ ብዙ ልምድ ያለው ብዙ ፈተናዎችን ያሳለፈ ግብጽ ዉስጥና ዉጭ ብዙ ተቀባይነት ያለው ድርጅት ነው፤ በ 1954 እነ ናስርና መካከለኛ የጦር መኮንኖች የተሳተፉበት መፈንቅለ መንግስት የግብጹን ንጉስ ሲገለብጡ ኢስላም ብራዘር ሁድ ከወጣት መኮንኖች ጋር ተባብሯል፤ ሲረጋጉ ግን ወታደሮች ኢስላም ወንድማማቾችን ገሸሽ አደረጓቸው፤ ወደ አመጽ ሲገቡ የናስር ቡድኖች የድርጅቱን ህጋዊነት አግደው እያሳደዱ አጠፏቸው፤ ኢስላም ብራዘርስ ድርጅት ዉስጥ ለዉስጥ መደራጀታቸዉን ቀጥለው ከህዝቡ አልፈው በ ፖሊስና በመከላከያ ሰራዊቱም መረባቸዉ ይዘረጉ ነበር፤ ናስርን የተካዉን ፕሬሲደንት ሳዳትን የገደሉት ወታደሩ ዉስጥ የተሰገሰጉት የ ኢስላም ወንድማማቾች አባላት ናቸው፤ ሙባረክ ሲተካ እያሳደደ ጨፈጨፋቸው፤ ግን እይጠፉም፤ የባሰ እያሰፉ እየጠነከሩ ሄዱ፤ ኢስላም ብራዘርስ ድርጅት ለኡሳማ ቢንላዲን አልቃይዳ ጠንክሮ መዉጣት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት የዚህ ድርጅት አባላት እንደሆኑ ይነገራል፤ ኦሳማ ቢንላደንን የተካዉ ያሁኑ የአልቃይዳው መሪ ግብጻዊዉ አይማን አልዛውሀሪ የዚሁ ድርጅት አባል ነበር::

የግብጽ ወጣቶች በሙባረክ ላይ ሲያምጹ ብዙ የግብጽን ሁኔታ የተከታተሉ ምሁራንና የፖለቲካ ተንታኞች ይህ ችግር ቶሎ እንደማይበርድና የከፋ እንደሚሆን ይገምቱ ነበር፤ ምክንያቱም ሶስት የማይጣጣሙ ሀይሎች ተሰልፈው ነበር 1ኛ የዲሞክራሲ ለዉጥ ፈላጊ ዘመናዊ ወጣቶች 2ኛ ኢስላም ወንድማማቾች ከፍተኛ መዋቅር ስላላቸው ልምድም ስላላቸው እድሉን ተጠቅመው ወደ ከፋ አመጽ ሊያስገቡት ይችላሉ መንግስትንም ሊቀሙ ይችላሉ፤ 3ኛ ጦር ሀይሉ ከ ኢስላም ወንድማማቾች ጋር የቆየ ቂም ስላለው ስልጣን ከያዙ ትላልቅ መኮንኖችን ሊያጠፏቸው ይችላሉ ስለዚህ ጦሩ የአመጽ ተሳታፊ ሆኖ እነሱን ሊጨፈልቅ ስለሚችል የተራዘመ የእርስ በርስ ጦርነት ይሆናል የሚል ነበር፤

እነመለስም ይህን ግምትና ስሌት ሳያሰላስሉት አልቀሩም፤ ለዚህ ይመስላል ሳያስቡት የግብጽ አመጽ እንደተጀመረ ወዲያዉኑ የአባይን ግድብ የጀመሩት፤ እንደተባለዉም ለ 2 አመት ግብጽ የሆነዉን አይተናል፤ የዉስጥ ችግር ቀለል አለ ሲባል የዉጭ ችግር መጣባት፤ ኳታርና ሳዉዲ እየተተካኩ ግራ አጋቧት፤

እንግዲህ የቱርክንም ግብጽንም የሳዉዲንም ችግሮችና ስጋቶች አይተናል፤ ሁሉም ይህን ችግራቸዉን ለመፍታት፤ የዉጭ ዘመቻ ከፍተዋል፤ ስትራቴጂ አጋር ፍለጋ ከዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ አልፈዉ ወታደራዊ ዘመቻም ጀምረዋል፤ ይህን ለማሳካት አጋር ፍለጋ ላይ ተጠምደዋል፤

**ውጥረቱ መባባስና የሳዉዲ ስልት።**

ሳዉዲ አራቢያ ኢራንን ለማሸነፍ ቀጥታ ሳይሆን የኢራን አጋሮች ማዳከም ይዛለች፤ የመን ስልጣን የያዘው ሁቲ መንግስት ዋና የኢራን አጋር ስለሆነች ሳዉዲ እነግብጽን ሱዳንን ጆርዳንን አራብ ኢምሬትን ኤርትራን አስተባብራ የመንን ከባለች፤ መናህሪያቸዉን አሰብ ላይ አድርገው የመን የሚገባና የሚወጣዉን ይቆጣጠራሉ፤ ደቡብ የመን ኤደን ወደብ የመሸገዉን የአብደልሀዲ አብድረቦ መንግስት እየደገፉ ሰሜኑን የመን ይደበድባሉ፤ አብደረቦ የመንን ለመቆጣጠር የራሱ ሀይል ደካማ ስለሆነ በሳዉዲ ጥሪ የዘመቱትን የነ ግብጽና ሱዳን ኢምሬትስ ወታደሮችን ይጠቀማል፤ እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ ኤርትራ ከኢራን ጋር ትሰራለች

ተብላ ትታማ ነበር፤ ኢራን ቀጥታ ወታደር ቀይ ባህር ላይ ባታሰፍርም የኳታር ጦር በጅቡቲና ኤርትራ መካከል በተፈጠረው ግጭት ሰላም አስከባሪ ተብሎ በሁለቱ ድንበሮች መካከል ቀይ ባህር ላይ ሰፍሮ ስለነበር ይህ ጦር ለኢራን የመረጃ ምንጭ ሳይሆን አልቀረም፤ የአካባቢዉ ቀውስ ሲጀመር ኤርትራ ከነኢራንና ኳታር አፈንግጣ ወደነ ሳዉዲና ግብጽ ወገነች፤ የኳታር ሰላም አስከባሪ ጦርም ነቅሎ አገሩ ገባ፤ በምትኩም በነሳዉዲና ግብጽ በሚመራው የሳዉዲና የአረብ ኢምሬትስ ጦር ሰፈረ፤ ቀይ ባህርም ሙሉ በሙሉ በሳዉዲ ጎራ በሚመራው ቡድን ቁጥጥር ስር ሆነ፤ በደርግ ግዜ አረቦች ቀይባህርን ለመቆጣጠር ይፈልጋሉ ይባል የነበረው እዉነት ሆኖ አሁን ሙሉ በሙሉ አረቦች ተቆጣጠሩት፤ ኢትዮጵያም ከበባው ውስጥ ገባች ማለት ነው።

**የቱርክ ስልት፤**

የኢራቅ ኩርዲስታኖች አገር ወደማወጅ እየሄዱ ስለሆነ በተለይ ምእራባዉያን በኩርዶች ላይ ከመለሳለስ አልፎ YPG የተባለዉ በሶርያ ኩርዶች የተጠናከረው አማጺ ቡድን ሰፊ ግዛት ከመቆጣጠር አልፎ በመራባዉያን በተለይ በአሜሪካ አሸባሪዎችን ይዋጋል በሚል ሰበብ ከፍተኛ ድጋፍ ስለሚደረግለት ለቱርክ ከባድ ስጋት ሆኗል፤ ቱርክ ይህንን የሉአላዊነት አደጋ ለመመከት ከኢራን ጋር እየተባበሩ ነው፤ ለቱርክ ስጋት የሆነባት ሀይማኖት ሳይሆን የሉዋላዊነት ስጋት ነው፤ አሁን የኢራቅ ኩርዶች ነጻ ወጡ ማለት ነገ ወደ ቱርክ ኩርዶች በዘመቱና ተመሳሳይ መነቃቃትና መፍጠሩ አይቀርም፤ ይህን ለመመከት ቱርክ አጋር አገራትን ለማስፋት ሱዳን ጋር ተስማምታ በቀይ ባህር ላይ ሰዋኪን የተባለ የጥንት ባዶ ወደብ ለመገንባትና ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት በሚል ሰሞኑን ተፈራርማለች፤ ይህ ነገር ከዛ አልፎ ወታደራዊ ተቋምም ሊሆን ይችላል በሚል ሳዉዲና ግብጽ አልወደዱትም፤ ቱርክ ከዛ እሩቅ መጥታ ቀይ ባህር ላይ ወታደራዉ ተቋም መገንባት ስጋት ሆነባቸዋል፤ ቱርክና ግብጽ የከረረ ኩርፊያ የጀመሩት በተለይ አብደልፈታህ አልሲሲ የብራዘርኍድ መሪዉን ሞሃመድ ሙርሲን በሳዉዲ ግፊትና ትብብር ገልብጦ ስልጣን ሲይዝ ክልፍልፍ የሚሉት የቱርኩ መሪ ኢርዶጋን በምሬት ተቃውመዉት ስለነበር ከዛን ግዜ ጀምሮ በቱርክና ግብጽ መሃከል መካረር ተጀመረ፤ ለዚህም የአጠፋ ምላሽ ጉለን የተባለው የቱርክ ቡድን በወታደሩ ተባባሪነት በኢርዶጋን ላይ ኩዴታ ሲያደርግ የ ግብጽ አበድልፈታህ አልሲሲ መንግስት ለገልባጮች የሞራል ድጋፍ አድርጎ ነበር፤ ኩዴታው ግን ከሸፈ፤ ኢርዶጋንም የግብጽ እጅ አለበት ብለው ገምተው ነበር፤ በኋላ ግን እጣታቸዉን ወደ መራባዉያን አዞሩት፤ ዞሮዞሮ ግብጽ ድጋፍ ስላሳየች ኢርዶጋን ቂማቸዉን አላወረዱም፤ ኩዴታዉን ለማክሸፍ ሲዋጉ ለተሰዉት የቀብር ስነስራእት በተገኙበት ሰአት ወደጋዜጠኞች ዞር ብለው የኢስላም ብራዘርሁድ ምልክት የሆነዉን 4 (አራት) እጣት ወደላይ በማድረግ የሰላምታ ምልክት አሳዩ፤ ያኔ ነበር የሲሲን መንግስት ጥርስ እንደነከሱበት የታወቀባቸው፤ ቱርክ ከዛም በላይ ኳታር የጦር ሀይል በማስፈር ለሳዉዲ ቀርብ ሆና ስጋት ዉስጥ ከታታለች፤ በሞግዚት የሚተዳደረው ደካማው የሞቃዲሾ መንግስትን የዚህ ተሳታፊነቱ ደርሶታል ቱርክ $500 ሚሊዮን የፈጀ የጦር ካምፕ ከፍታለች፤ የኦቶማን ኢምፓየር እንደገና ሊመጣ ይሆን?

**ግብጽና ወያኔ**

በአባይ ግድብ ዙሪያ በሚደረግ ድርድር ለግብጽ ወያኔ የማይጨበጥ ወስላታ ሆኖበታል፤ በድርድር ሰበብ ግዜ እየገዛ እንደሆነ ተገንዝበዋል፤ ግድቡንም በፍጥነት እያጣደፉት እንደሆነ ለጋራ ስምምነትም ፍላጎትም ሆነ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ገብቶታል፤ የሱዳን መንግስት ኡመር አልበሽር ከወያኔ ጋር ወግኖ የአባይን ግድብ በይፋ መደገፉ ግብጽን እርር ድብን አድርጓቸዋል፤ ግብጽ ያላት መፍትሄ ወታደራዊ ዘመቻ ብቻ እንደሆነ ገብቷታል፤ ግን በየት አድርጋ ጦርነት ትግባ?. ሱዳን ከግብጽ ጋር ብትተባበር ያለምንም ጥይት ከሱዳን 40 ኪሎሜትር ረጅም መድፍ ወይም ሮኬት ጠምዶ በማስፈራራት እንድም ጥይት ሳትተኩስ ግድቡን የሚሰሩ የዉጭ አገር ዜጎች ጠቅልለው ይወጣሉ፤ ግድቡም ያቆማል፤ no war no peace እንደተባለው no war no dam constrction ይሆናል፤

አሁን ግብጽ ሁለት አማራጭ ይዛ እየሰራች ይመስላል፤ 1ኛ ከኤርትራ ጋር በይፋ በመተባበር በወያኔ ላይ ጦርነት መክፈት፤ ሁለቱም ኢትዮጵያ ላይ የጋራ ጥቅም አላቸው፤ ጥቅማቸዉንም ወያኔ ነው የዘጋባቸው፤ ስለዚህ ወያኔን ከእጃዙር አልፎ በቀጥታ ተሳትፎ ማስወገድ፤

2ኛ ግብጽ አልበሽርን ከስልጣን ማስወገድ። የሱዳን የጦር ሀይል ከፍተኛ መኮንኖችና አንዳንድ ባለስልጣኖች የተማሩት ግብጽ ነው፤ አልበሽር የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ሳያበላሸው በፊት የሱዳን ከፍተኛ ባለስልጣኖችና ጄኔራሎች ለእረፍት ወጣ የሚሉት ወደ ግብጽ ነበር፤ ያ ማለት የግብጽ የስለላና ደህንነት መዋቅር የሱዳን ጄኔራሎችንና ባለስልጣኖችን ባህሪ አቅምና ፍላጎት በደንብ ይረዱታል ብየ አስባለሁ፤ ስለዚህ ከአንዳንዶች ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል፤ ይህን ትዉዉቅ ተጠቅሞ እየጃጀ የመጣዉን አልበሽርን በኩዴታ ሊያስወግዱት የሚችሉበት ሁኔታ ያለ ይመስላል፤ 2ኛ ሱዳን ዉስጥ የቀዘቀዘዉን አራብ ጸደይ በማስነሳት በህዝባዊ አመጽ አልበሽርን ሊያስወግዱት ይችላሉ፤ የዳርፎር እና የጀበል ኑባ አማጽያንን በመርዳት የአልበሽር መንግስት በጦርነት እንዲወጠርና የዉስጥ አመጹ እንዲባባስ ሊያደርጉም ይችላሉ፤ ለግብጽ ለዚህ እቅዳቸው እነሳዉዲና አራብ ኢምሬትስ ከፍተኛ ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ፤ ምክንያቱም እርዳታ ሳይሆን ዉለታ ምለሳ ወይም መተጋገዝ ነዉና፤ ግብጽ ኢራንን ለመመከት የመን ላይ ጦር ስላዘመተች እነሱ ደሞ ወታደር መስጠት ባይችሉ እንኳ የፖለቲካ የዲፕሎማሲና የሎጀስቲካ ድጋፍ ያደርጋሉ፤ በዲፕሎማሲው ድጋፍ እነ ሳዉዲ ኤርትራ ሙሉ ትብብር ከግብጽ ጋር እንድታደርግ ገንዘብም እንደሚሰጣት ተጽኖ ያደርጋሉ፤ ሱዳንንም አልበሽር ከወያኔ ተላቆ ከግብጽ አረብ ወንድሞቹ ጋር እንዲወግን ካልሆነ ግን እነሳዉዲ ማንኛዉንም ተጽኖ ለማድረግ ከግብጽ ጋር እንደሚተባበሩ ያስገድዳቸዋል፤

## ኳታር ችግርና ተሳትፎ

በጋዝ ሀብት የምትታወቀው ኳታር ምንም አይነት ስጋት የለላባት፤ ዝምብላ በገንዘቧ በብዙ አገሮች ዉስጥ እጇን በማስገባት ተጽኖ ለመፍጠርና የእሷ ወዳጅ የሆነ መንግስት ለመትከል ብዙ ትጥራለች፤ ለማስረጃም በጋዳፊ ላይ የተነሳዉን ህዝባዊ አመጽ ቀደም ብሎ ተቃዋሚ ግለሰቦችን እያግባባች እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ሞሀመድ ሙርሲንም ከጅምሩ ስትደግፍ እንደነበር ይታወቃል፤ ኤርትራን በተለያዩ የኢኮኖሞና ገንዘብ ወጭወች ታግዝ እንደነብረ ይታወቃል፤ የኤርትራዉ ፕሬዚደንት ለስራ ጉዳይ ወደ ዉጭ ለሚያደርጉት ጉዞ የኳታር አየር መንገድ በልዩ ትዛዝ እየተላከለት ነበር የሚንቀስቀስ፤ የሰሜን ሱዳንን

የዳርፎር አማጽያንን ከአልበሽር መንግስት ጋር ለማስታረቅ ላለፉት 6-8 አመታት ሙሉ ወጪአቸዉን በመሸፈን አገሯ እየጋበዘች ተከታታይ ድርድር ሲያደርጉ ቆይተዋል፣ አሁንም እንደቀጠለ ነው፤ የኳታርን መንግስት የመቻቻል የስልጣኔ ይበሉት ወይም የጥቅም ከሌሎች አረብ አገሮች ለየት የሚያደርጋት ነገር አለ፤ በመወያየትና በመቀራረብ መነጋገርና ችግሮችን መፍታት የሚል ቅንነት የተሞላበት እዉነት ሰላም ፈላጊ የሚመስል ስራ ስትሰራ ታይቷል፤ ለዚህም ማሳያ አረቦች አይኗን ላፈር ያሏትን እስራኤልን በ 1996 መጨረሻ በአካባቢዉ ሰላም ለማምጣት ለእስራኤል ዋስትና ልንሰጣት ይገባል የሰላምና የመቀራረብ ስራዎችና ንግግሮች መደረግ አለበት በሚል ከእስራኤል ጋር የንግድ ልዉውጥ ለማድረግ እስራኤል የንግድ ቢሮ በ ዶሀ መክፈቷ አለምን ያስደመመ አረቦችን ያስቆጣ ሆኖ ነበር፤ ይባሱንም የእስራኤል የንግድ ሚኒስቴር ተጋብዞ ኳታርን ጎብኝቶ ነበር፤ ሌላዉ የኳታር ለየት ያለ አካሄድ ሽብርተኛን ለመዋጋትና ሰላም ለማስፈን የአፍጋኒስታን መንግስት ከታሊባን ጋር ለምን ድርድር አያደርግም ብላ በራሷ ተነሳሽነት ታሊባንና የአፍጋን መንግስትን ለማደራደር ዶሀ ለታሊባን በራሷ ወጭ ቢሮ ከፍታ ቋሚ የታሊባን ተደራዳሪዎች ዶሀ እየኖሩ የተወሰኑ ዙር ድርድሮች አድርገው ነበር፤ ይህ ሁሉ ድርጊቷ ከተወሰኑ አገሮች ጋር ወዳጅነት ስታፈራ ከተወሰኑት ጋር ደግሞ የመረረ ጠላትነት ፈጥራለች፣ ኳታር የሱኒ ሀይማኖት ተከታይ ብትሆንም ገዥው ንጉሳዊ ቤተሰብ የ እስላምብራዘርሁድ ቡድንን ፍልስፍና እንደሚደግፍ ይነገራል፤ ለየት ሲል ደግሞ ከአረብ አገራት በተለየ መልኩ በነጻነት የመናገር መብት ፈቅዳ አልጀዚራ የሚባል ቴሌቪዥን ከፍታ ከምራባዉያን አቻ አቀራረብ ሁሉንም የአረብ አገራት በግልጽ ሲተችና ሲዘግብ የገልፍ አገሮች አልወደዱትም ነበር፣ የገልፍ አገራት በተለይ ሳዉዲና ኩዌት ግብጽን ጨምሮ አልጀዚራ የአረቦችን ምስጢር እያወጣ እያዋረደን ነው ለምን አትዘጉትም በሚል ከኳታር ጋር ገና በ ዘጠንዎቹ ነው ጭቅጭቅ ዉስጥ የገቡት፣ ለዚህ ክስ የኳታር መንግስት መልስ አልጀዚራ ዉሸት ዘግቦ ከሆነ የዘገበዉን ጋዜጠኛ ክሰሱት እንቀጣዋለን እዉነት ዘግቦ ከሆነ ምንም ማድረግ አንችልም ይሉ ነበር፤ ኳታሮች አልጀዚራን ለአረቡ ገዢ ቡድን ሳይሆን ለአረቡ ህዝብ እንደ መማሪያና ስልጣኔ መንገድ ይከፍታል ሚዲያ ለእድገትና ስልጣኔ ወሳኝ ነው የሚል እምነት ነበራቸው። ነገሮ በግልጽ እየተባባሱ የመጡት ኳታር የ መሃመድ ሙርሲን መመረጥ ደግፋ ስትቆም በሳዉዲ የሚመራው የአረቦች ስብስብ በጣም አኮረፉ፤ ሙሃመድ ሙርሲ እንደተመረጠና ስልጣን ሲረከብ ካታር ለሁለት አመት በህዝባዊ አመጽ የደቀቀዉን የግብጽን ኢኮኖሚ ለመደገፍ አስር ቢሊዬን ዶላር ለሙርሲ መንግስት ሰጠች፤ ሳዉዲዎች የባሰ አበዱ፤ ከአሜሪካኖች ጋእ በመመካከር አብደልፈታህ ሲሲን ጨቅጭቀው ሙርሲን አስገለበጡት፤ ካታር ለህገወጥ ወታደራዊ መንግስት አልሰጥም ብላ ያሰጠችዉን ገንዘብ በአመቱ መልሳ ስትወስድ ሳዉዲ አስር ኢሚሬትስ አምስት አድርገው ባጠቃላይ አስራ አምስት ቢሊዮን ዶላር ለአልሲሲ መንግስት ሰጡት፤ ጥላቸው በይፋ ሆነ።

እነ እነሳዉዲ በኢራን ላይ የዲፕሎማሲ ጦርነት ዘመቻ ሲጀምሩ ኳታር ከነኢራን ጋር ያላትን ወዳጅነት እንድታቋርጥ በሳዉዲዉ ጎራ ብትለመን ከእሩቅ ወዳጅ የቅርብ ጠላት ይሻላል፣ አፍንጫችን ስር ያለችው ኢራን ጋር መነጋገርና ችግሩን በሰላም መፍታት አለብን በማለት አሻፈረኝ አለች፤ ይህ የጸና አቋሟና እምነቷ ከሌሎች የቆዩ ቁርሾሞች ጋር ተደምሮ ነገሩን አባባሰው፤ እንዘዚያ በሳዉዲ የሚመሩት የገልፍ ቡድኖችና ሌሎች የጥቅም ተሰላፊ አገሮችን ጨምሮ በኳታር ላይ ጦር የቀረው ዘመቻ ከፈቱባት፤ ከፍተኛ የተባለ ማእቀብም ጣሉባት፤ የንግድ የጉዞ የአየርና የባህር እገዳ ጣሉባት፤ አብዛኛዉን ምግብ ፍጆታ ከዉጭ

ስለምታስገባ ኢራንና ቱርክ ለዚህ ፈጥኖ ደራሽ ሆነው በአየር እያጓጉዘው ደረሱላት፤ የሳዉዲን ቡድን የባሰ አስቆጣ፤ ይባስ ብሎ ወታደራዊ ጥቃት ያደርጋሉ ተብሎ ስለተሰጋ ችኩሉ የቱርክ መሪ ኢርዶጋን ብዙ ሺህ ጦር ልኮ ኳታር ዉስጥ ጦር በማስፈር እረመጡን ወደፍም ለመቀየር እየሞከረ ነው፤

በአካባቢው እየተገለለች የመጣችው ኳታር ገንዘቧን በመጠቀም እሷም እንደአቅሟ አጋር ፍለጋ ወጣ ብላለች፤ ለዚህም በአሁኑ ወቅት ምቹ ሆና የተገኘችዉ አንዷ ኢትዮጵያ ናት፤ ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር ሊፈታ የማይችል ቅራኔ ውስጥ ስላለች ኳታር ደግሞ ከግብጽ ጋር ቂም ስላላት በእልክ ከኢትዮጵያ ጋር ወግና ግብጽን ለማጥቃት ይመስላል፤ ለዚህም ወያኔ እንደጭራቅ ከኢትዮጵያ ያባረረዉን አልጀዚራን እንደገና ሳይታሰብ September 2017 እራሱ ወያኔ ጠርቶ በአፍሪካ ትልቁ የተባለዉን ስቱዲዮ በአዲስ አበባ ከፈተ፤ የአልጀዚራ አዲስ አበባ መከፈት የቸኮላ የውያኔ የፖለቲካ ዉሳኔ መሆኑን የሚያሳይ ነገር አለ፤ በመክፈቻ ምረቃ ላይ የክብር እንግዳ ሆነ የተገኘው ስብሀት ነጋ ነበር፤ በመንግስት መዋቅር ስልጣን ሳይኖረው አገር ይመራል ተብሎ የሚታወቀው ስብሀት ነጋ በይፋ ቋሚ ስራው የኢትዪጵያ የሰላምና የልማት ኢንስቲቱት የሚባለዉን መስሪያ ቤት በዳሬክተርነት ይመራል፤ በዚህ በኩል ሳይሆን አይቀርም አልጀዚራ ተመልሶ ወደኢትዮጵያ የመጣው፤

**ትንሽ ስለ ስብሀት ነጋ እና ስለ ስዉሩ መስሪያ ቤት፤**

የኢትዮጵያ የሰላምና የልማት ኢንስቲቱት መስሪያቤት በዋናነት ድብቅ ስራው የኢትዮጵያ የዉጭ ፖሊሲ እንዴትና ምን መሆን እንዳለበት ጥናት አጥንቶና የአፈጻጸምና አስፈጻሚ እቅድ አዉጥቶ በህወሀት መዋቅር ለአገዛዙ በማቅረብ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ነው፤ አምባሳደር ሆነው የሚሾሙ ግለሰቦችን በስዉር የሚያጭና የሚመድብ ይህ መስሪያ ቤት ነው፤ ይህ ቢሮ ያዘጋጀዉን ለአገዛዙ በህወሀት መዋቅር ያቀርብና ሆዳም ባንዳ ባለስልጣን ተብየወች በደብዳቤ ይነገራቸዋል፤ የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ ደሞ ዋና ትኩረቱ ህወሀትን ስልጣን ላይ ሊያቆይ የሚችል ፖሊሲ መንደፍ እንጂ አገሪቱን የሚጠቅም አደለም፤ ይህን መስሪያ ቤት ከአሁን በፊት ዶ/ር ክንፈ አብርሀ ነበር የሚመራው፤ ክንፈ አብርሀ እስከለተ ሞቱ ድረስ ዋና የህወሀት የዉጭ ፖሊሲ ነዳፊ የመለስ ቀኝ እጅ ነበር፤ በ2006 ወያኔ ሶማሌን በድንገት የወረረው የክንፈ ምክር እንደነበር ብዙዎች ይስማማሉ፤ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ላይ ትንሽ ከቆዩ ለኦሮሚያ ድንበርተኛ ስለሆነች ኦነግና ኦብነግ ቶሎ ወደመጠናከር ይሄዳሉ፤ ብዙ የኦሮሞ ወጣቶች በሰአታት ጉዞ እያቋረጡ ሶማሊያ በመግባት ኦነግና ኦብነግ በቶሎ የማይቆረጠሙ የብረት ቆሎ ሊሆኑ ይችላሉ ስለዚህ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች የሚባለው መንግስት ሳይጠናከር ባስቸኳይ እናስወግደው በሚል ያልታሰበ ዘመቻ አድርገው ይህን መንግስት ደምሠው ብዙ ሰባዊ መብት ጥሰው ሶማሊያን በተኗት፤ ለዚህም አልሸባብ እንዲፈጠር በር ከፈተ፤ በኤርትራ በኩል ካሁን በኋላ ስጋት የለም ምንም ወደጦርነት የሚያስገባን ነገር የለም የሚለዉን ጥናትም የአገዛዙ ፖሊሲ እንዲሆን የሆነው የዚህ የስብሀት ቢሮ ጥናት ነው፤ ስለዚህ ይህ የኢትዮጵያ የሰላምና ልማት ኢንስቲቱት የሚባለው ቢሮ እጅግ ከባድ የጥፋት ቢሎ ነው፤ አልጀዚራንም ሳይታሰብ አዲስ አበባ ቢሮ እንዲከፍት ያደረገው የዚህ መስሪያ ቤትና ስብሀት ስራ ነው የሚል እምነትና ፍንጮች አሉ፤ ስለዚህ ኳታር ምንም ችግር ሳይኖርባት እየዞረች የሌሎችን ችግር ለመፍታት ስትል እራሷ ችግር ዉስጥ የገባች አገር ናት፤

ይህ ሁሉ ያንዣበበ አደጋ ኢትዮጵያን ወዴት ይወስድታል? ግብጾች የአባይን ግድብ በማስቆም ወይም በማፍረስ ብቻ ያቆማሉ? ዘመቻቸው ይህ ብቻ ይሆናል? ኤርትራስ ባድሜን ማግኘት ብቻ ይሆናል? ኢትዮጵያ ወዴት ትሄድ ይሆን?

አደጋ አደጋ! አንድ ቀን ወዳልታሰበ እጅግ የከፋ አደጋ እንዳይወስዳት።

አለማቀፍ ህግ የሚሰራው የምትከበር የምትፈራ አገርና መንግስት ሲኖርህ ነው፣ ትልቅነት ወይም መከበር በወታደራዊ ወይም በኢኮኖሚ ሊሆን ይችላል፣ ካልሆነ ግን ቢያስ አንድነቱ የጠነከረ ጠንካራ ህዝብና መንግስት ሊኖርህ ይገባል፤ ይህ ካለህ ያንተ ያልሆነ የማይገባህንም በመቀማትም ታገኛለህ፤ ደካማ ከሆንክ ያለህም ይወሰድብሀል፤ ይህን የአለም ገሀድ አሳይቶናል፤ ቻይና በወታደራዊም በገንዘብም በህዝቧ አንድነትም ጠንካራ ስለሆነች ከ 160 አመት በኋላ ሆንግኮንግን ከእንግሊዝ በ1997 አስመልሳለች፤ ማካዉ የተባለችዉን ትንሽ የባህር ዳርቻ ግዛትከ442 አመት በኋላ በ 1999 ዓ/ም ከፖርቱጋል አስመልሳለች፣ ቻይና በ አፍሪካ አገሮች ላይ ተጽኖ በማድረግ ታይዋን በሁሉም አፍሪካ አገሮች እንደ ነጻ አገር እንዳይቆጥሯትና ኢምባሲ እንዳትከፍት አድርጋለች፤ ሩሲያ የዩክራይን ትልቅ ወደብ ያለበትን የክሪሚያ ግዛትን ከ150 እመት በኋላ የኔ ነው ብላ በቅርቡ ወስዳለች፤ እኛ ግን የነበረን ወታደራዊም ኢኮኖሚያዊም ተዳክሞ ምንም ታሪካዊ ማስረጃ የለላቸው የኢትዮጵያ ግዛቶች እየተወሰዱብን ነው ወደፊትም የሚሄዱ ያሉ ይመስላል፤ ወኔ አልባ ለሀገር ሉዋላዊነት ግድ የሌለው እንዲያዉም ለስልጣኑ ሲል ሉዋላዊነትን አሳልፎ የሚሰጥ ወራሪ ባንዳ አገዛዝ ነው ያለን፤ ይህን ያንዣበበ ከባድ ጦርነት አደጋ እንኩዋን መቋቋም ይችል የሆን? ችግሩ ወያኔ በጣም ፈሪ ስለሆነ የአገራችን ሉዋላዊነት አደጋ ላይ ጥሎታል ለስልጣኑ ሲልም አሳልፎ መስጠቱ ያሰጋል፤

## በዚህ ግርግር የእስራኤል ተሳትፎ ምን ይሆናል?

እስራኤል አባይን ለመጠቀም ከፍተኛ ፍላጎት አላት፤ በ 1903 አካባቢ ጀምሮ እስራኤል ለመመስረት ባዶ መሬት እንዲፈልጉ የተላኩት የጽዮናዉያን ቡድኖች ሲና በረሀ ምንም ሰው ስለማይኖርበት ህዝባችን ማስፈር እንችላለን ብለዉ አቅደው ነበር፤ ይህን ቦታ ለማጥናት ሰወች ተልከው ሲና በረሀን ጎበኙት፤ ምንም ዉሀ ስለሌለ ሰው ሊኖርበት እንደማይችል ተረዱ፤ እንደ አማራጭ ግን የአባይን ወንዝ ቦይ ሰርቶ ሲና ማድረስ እንደሚቻል ሀሳብ አቀረቡ፤ ነገሩ ግን በወቅቱ ከባድ ነበር፤ የአካባቢዉ ሁኔታ በፍጥነት ስለተለዋወጠ እቅዱ እንዳይረሳ ሆኖ ተዳፈነ፤

ከግብጽ ነጻነት በሁዋላ እና እስራኤልም እንደሀገር ከተመሰረተች በኋላ ዉስጥለዉስጥና ባደባባይ እኛ ችላ ያልናቸው በአባይ ጉዳይ ከባድ ነገሮች ተከስተው ነበር፤ የግብጹ ፕሬስደንት አንዋር ሳዳት እስራኤልን ለማባበል ብለው አባይን እስከ እየሩስ አለም ለማድረስ ባደባባይ ለእስራኤል ቃል ገብተው ነበር፤ ይህን የሚያደርጉት ደሞ እስራኤል ከኢትዮጵያ ጋር አባይን ለመገደብ እንዳትተባበር ነበር፤ በተግባር ለማዋል ግን የአረቦችና የዉስጥ ተጽኖ በዝቶባቸው ወደተግባሩ መግባት ይዳዳቸው ነበር፤ እስራኤልም አባይ ሲና በረሀን አቋርጦ እንዲደርሳት ትፈልግ ነበር፤ ለማስፈራራትና በግብጽላይ ለተጽኖ ለማድረግ ከንጉስ ሀይለስላሴ ጋር በመተባበር ወታደራዊ እርዳታ ታደርግ ነበር፤

በ1997 የግብጽ መንግስትም ለራሱ ጥቅም ብሎ ሲና በረሀን ለማልማት ከፍተኛ ወጭ አዉጥቶ አባይን አቅጣጫ አስቀይሮ በ 1997 ሲና በረሃ አደረሰው፤ አለምን ያስደመመ 3ሚሊዮን ህዝብ የሚሰፍርበትና የሚያርሰው ልማት ከፈተ፤ አባይ ልክ ከእስራኤል ድንበር 40 ኪሎሜትር እርቀት ላይ ይገኛል፤ በዉሀ እጥረት የምትሰቃየው እስራኤልንና ጆርዳን የተንጣለለዉን አባይን ከማዶ እያዩ እንቁጭልጭ እያለች ነው፤ እስራኤልም ከዚህ በመቀጠል አባይን ለመጠቀም ከግብጽ ጋር ዉይይት ጀምራ ነበር፤ ከድንበሯ 40 ኪሎሜትር የደረሰዉን አባይን እስራኤል ለማድረስ ሙባረክ ፈራ ተባ እያለ ስላስቸገራቸው እስራኤሎች ልትዮጵያ በአባይ ላይ ግድብ ለማሰራት ከፍተኛ የዉሀ ባለሙያዎች ወደ ኢትዮጵያ ብቅእልም እንዲሉ ማድረግ ጀምራ ነበር፤ ይህን የሰማው ሙባረክ 1997 የሲናን በይ ሲከፍት በድንጋጤ ለእስራኤሎችን ትልቁን የአባይ በይ እየሩስ አለም ለማድረስ ቃል ገባ፤ በወቅቱ መለስ ዜናዊ ይህን ነገር ባደባባይ ተቃዉሞ ነበር፤ የሚገርመዉ በዚያን ወቅት ሳዉዲ አራቢያና ጆርዳንም የአባይን በይ አስፈላጊዉን ወጭ ከፍለው ወደነሱም ግዛት ለማስገባት ጥያቄ አቅርበዉ ነበር፤ እስራኤል አባይን ለመጠቀም ከግብጽ ጋር መወገኗ አይቀርም፤ ሁሌም እንደሌሎች አገሮች የብሄራዊ ጥቅሟን ነው የምታስቀድመዉ፤ ለኢትዮጵያ የምታደላበት አንድም ነገር የላትም፤ በታሪክም በግልጽ ስትረዳንም ስትከዳንም ነው የምናውቀው፤ ለምሳሌ ንጉሱ ኅይለስላሴ ማንዴላን ለማሰልጠን አዲስ አበባ ባስመጡበት ጊዜ ጥንቃቄ ሲደረግለት የነበረው እንግሊዝና እስራኤል እንዳይሰሙ ነበር፤ ከሰሙ ሊገድሉት ስለሚችል ነበር፤ 2ኛ ወያኔ በባድሜ ሰበብ ከሻብያ ጋር በተዋጋበት ግዜ እስራኤል በኢትዮጵያ ላይ ታሪካዊ ክህደት ፈጽማለች፤ ነገሩ እንዲህ ነው፤ ጦርነቱ አይቀሬ መሆኑን የተረዱት የወያኔ መሪዎች ሚግ 21 ተዋጊ ጀት ደረጃቸዉን ከፍ (upgrade) ለማድረግ ወደ እስራኤል ተልከው ነበር፤ የመጀመሪያው ዙር ጦርነት ፈንድቶ ለሁለተኛዉና ለዋናው ጦርነት ዝግጅት ሲጀመር ሚግ ጀቶች ተሰርተው አልቀው ነበር፤ የወያኔ ባለስልጣናት ሊረከቡ ሲሄዱ የእስራኤል መንግስት አልሰጥም አለ፤ ብዙ ዉዝግብ ደረሰ፤ የእስራኤል ባደባባይ ጀቶችን የማንሰጠው በሁለቱ ተዋጊ አገሮች ላይ የሀይል ሚዛን ልዩነት ስለሚያመጣ ነው በማለት ለኤርትራ ወገንተኝነቱን ተናገረ፤ ስለዚህ ጦርነቱ እስከሚያቆም መልሰን አንሰጥም አሉ፤ ለነገሩ ወያኔ እራሱን ለማዳን የማይወጣዉና የማይወርደው የለምና ወዲያው በእጅጉ ከ ሚግ 21 እና 23 የሚበልጥ ዘመናዊ SU 27 ጄት ገዝቶ ጦርነት ውስጥ ገባ፤ ስለዚህ እስራኤል አባይ 40 ኪሜ ደጃፏ ላይ ነው ያለው፣ ለመጠቀም ያላት እድልና ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ነዉ ስለዚህ ኢትዮጵያ አባይን እንድትገድብ በድብቅም ሆነ በግልጽ ልትቃወም ትችላለች፤

## አህባሽ እስልምና አስተምሮት፤ሳዉዲና አረቦች የሚታገሉት ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለ ከባድ ነገር።

አህባሽ የሚለዉን የእስልምና ቡድን መጀመሪያ የሰማሁት በ 1999 አካባቢ ለስራ መካከለኛው ምስራቅ በምንቀሳቀስበት ግዜ ነው፤ የሊባኖን ቤሩት ዜጎች የሆኑ አብረን ባንድ መስሪያ ቤት እንሰራ ነበር፣ በነበረን መልካም ግንኙነት እንግባባ ነበር፤ በተለይ ሁለቱ ለኔ ለየት ያለ የወንድምነት አመለካከት ነበራቸው፤ በተደጋጋሚ ስለ አብዳላ አልሀረሪ ይጠይቁኛል፤ እንደዚ የሚባል ሰው አላዉቅም አልኳቸው፤ ተናደዱብኝ፤ ግራ ገባኝ. ሁሌም ይጠይቁኛል፤ የነሱ ጓደኞች እንዳይሰሙ ይጠነቀቁ ነበር፤ አንድቀን ቁጭ ብለን በሰፊው አወራን፤ አንተ ኢትዮጵያዊ ሆነህ እንዴት ሼህ አብደላ አልሃረሪን አታዉቅም? እሳቸው እኮ በዘመናችን አሉ የተባሉ ሊቅ ናቸው አሉኝ፤ ከኢትዮጵያ ከሃረር ወደ ሊባኖን ድሮ እንደሄዱ አህባሽ የሚባልና እስልምና መሪ

እንደሆኑ ሊባኖስ አገር አብደላ አልሃረሪ ማለት በጣም የታወቁ እንደሆኑ ብዙ ሰወች ግን እሳቸዉንና የሳቸዉ ተከታዮችን ለማጥፋት እንደሚሞክሩ የሚሉ ብዙ ነገሮችን አስረዱኝ፤ እኔም አላዉቃቸዉም ስል ሆን ብዬ እሳቸዉን የምቃወም መስሏቸው ገሸሽ ማድረግ ጀምረው ነበር፤ ባጠቃላይ የሚሉት ነገር ስላልገባኝ ነገሩን ተዉኩት እረሳሁት፤

አብደላ አልሀረሪ በሀረር ከተማ የተወለዱ የአዴሬ ተወላጅ ናቸው፤ በንጉሱ ግዜ ትንሽ ለየት ያለ የእስልምና አመለካከት ያራምዱና ያስተምሩ ስለነበር ከሌሎች ሙስሊሞች ጋር ባለመስማማታቸው ተጽኖ ስለበዛባቸው የተሰደዱ ናቸው፤ በደርግ ግዜም ወደ አገራቸው ተመልሰው ደርጉ መልሶ አባረራቸው ይባላል፤ እኒህ ሰው የሳቸዉን ለየት ያለ እስልምና አመለካከት የሚጋሩ ብዙ ሰወች በሊባኖስ ስላገኙ በተደራጀ መልኩ አዋቅረው እሳቸዉን የመጀመሪያው የቡድኑ መሪ አድርጎ በመምረጥ ትምህርት በመስጠ ብዙሺህ ተከታይ አፍርተዋል፤ ከቁርአን ትንሽ ወጣ ያለ ትምህርት ይሰጣሉ፤ ለሴቶች ለቀቅ ያለ ነጻነት ይሰጣሉ ሴቶች ሶላት እንዲመሩ ይፈቅዳሉ፤ ሙስሊም ካልሆነ ሰው ጋር በነጻነት አብሮ መኖርንና መቻቻልን ያስተምራሉ፤ ይህ የሳቸው አመለካከት ከሊባኖን ወጥቶ በተወሰኑ አፍሪካ አገሮች በተለይ እንደ ናይጄሪያና ሴኔጋል እንዲሁም በመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ብቅብቅ እያሉ ነው፤ ስሙም **አህባሽ** ይባላል፤ ሀበሻ እንደማለት ነው. መስራቹ ሼክ አብደላ አልሀበሺ ወይም አልሀረሪ ስለሆኑ ነው የቡድኑ ስም አህባሽ የተባለው ይባላል፤ ከሱኒና ሺአ የተቀየጠ ይመስላል፤ ሰለፊ የሚባለዉን ቡድን ጋር ይመሳሰላልል ወይም ያጠናክራል፤ እንግዲህ ሱኒ ሺአ ሰለፊ ሱፊ እንደሚባሉት አሁን ደሞ አህባሽ ተጀምሯል፤

### አብደላ አልሀረሪን ወይም የሳቸዉን የእስልምና አመለካከት አስተምሮ ሌሎች ሱኒ ተከታዮች በተለይ ሳዉዲ አራቢያ ለምን እጅግ በጣም ይቃወሙታል?

የአህባሽ አስተምህሮ የሚቃወሙት ሙስሊሞች አህባሽ ቁርአንን ይዳፈራል ከቁርአን ትንሽ ወጣ ያለ ትምህርት ያስተምራል ይላሉ፤ ካይሮ የሚገኘው አል-አዝሀር መስጂድ አህባሽን አዉግዞታል፤ ከሀዲነው ሁሉም ሙስሊም ሊያወግዘው ይገባል ብሏል፤ አል-አህዛር ዩኒቨርስቲ በሙስሊሙ አለም እጅግ የተከበረ ብዙ ልሂቃንን ያፈራ ዩኒቨርስቲ ነው፤ መስጊዱም በተመሰከረላቸው የሙስሊም ኡለማዎች ነው የሚመራው፤ ከዚህ መስጊድ የሚዎጡ መመሪያዎችና ጽሁፎች በጣም ተቀባይነት አላቸው፤

በተለይ **አህባሽ** ከባድ ግጭት ያለበት ከአል-ሳዉድ ጎሳ የሆነው የሳዉዲ ንጉሳዊ ቤተሰብ ጋር ነው፤ አህባሽ ስለ ቅዱስ መስጊዱ መካ እና መዲና መስጂዶች የአስተዳደር ስልጣን ጠንከር ያለ ትችት ይተቻል፤ ንጉሳዉያኑ ቤተሰብ እጃቸዉን ከቅዱስ መስጂዶች ማንሳት አለባቸዉ ይላል፤ ሁልግዜ የሁለቱ ቅዱስ መስጂዶች የበላይ ጠባቂ የሳዉዲው ንጉስ ነው፤ የሳዉዲ ንጉስ ሲጠራ “ካድም ሀራማይን ሸርፌይን” ይባላል፤ ይህ ማለት የሁለቱ ቅዱስ መስጂዶች አገልጋይ ማለት ነው። ታዲያ **አህባሽ** አስተምሮ ንጉሱ ይህን ትልቅ ስልጣን መያዝ የለበትም ይላሉ፤ መከራከሪያቸዉም ንጉሳዊያን ቤተሰቦች ይባልጋሉ ብዙ ስህተት ይሰራሉ አኗኗራቸው ከህዝበ ሙስሊሙ የተሰወረ ና ዘመናዊ ነው በሀብታቸው በዉጭም በአገራቸዉም ብዙ እስልምናን የሚጻረር ነገሮችን ይሰራሉ ስለዚህ እነሱ ማስተዳደር የለበቻዉም ይላል፤ ካድም ሀረማይን ሸርፌይን (የሁለቱ መስጂዶች) አገልጋይ ወይም የበላይ ጠባቂ መሆን ያለበት ህዝብ ያወቀዉ በእስልምና

ጥልቅ እዉቀት ያለዉ ለህዝበ ሙስሊሙ ግልጽ የሆነ ሰው መሆን አለበት ይላሉ፤ በነገራች ላይ ይህን አባባል ሺአ ኢራንም ትጋራለች፤ እንዲያዉም ያከሩታል፤

በማስረጃ ባይረጋገጥም ከአህባሽ ጀርባ እስራኤልና አሜሪካ አሉበት ይባላል፤ አህባሽ የአንድ ሀገር የእስልምና መጅሊስን ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠረው ለመጀመሪያ ግዜ አሁን በወያኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፤ በሌላ አገር እንኩዋን መጅሊሱ ዉስጥ ሊገባ ከሊባኖስ ዉጪ በሙሉ ነጻነት እንኳ አይንቀሳቀሱም፤ ወያኔ **አህባሽን** አስፋፋ ማለት በሳዉዲ ንጉሳዉያን ቤተሰቦችና መንግስት ላይ የህልዉና መፈታተን ነው፤ ከዛም አልፎ አጠቃላይ የሱኒ ሙስሊም ተከታዮችን መፈታተን ነው፤ ስለዚህ ሳዉዲ አራቢያ ወያኔን ለማስወገድ ካገኘችዉ ሀይል ጋር መተባበሯ አይቀርም፤ ወያኔን አፈረስን ሲሉ ያዉ ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው፤ ለዚህም ሶስቱ ግብጽ ኤርትራ ሳዉዲ በኢትዮጵያ ላይ የጋራ ጥቅም ስላላቸው መተባበራቸው አይቀርም፤ ሁሉም ወያኔን በማፍረሱ ላይ የተለያየ አሰላለፍ አስተዋጽዎ ይኖራቸዋል፤ ኤርትራ መሬቷንና ጦሯን ታሰልፋለች፤ ግብጽ ጠንካራ አየርሀይሏንና እግረኛ ጦሯን የሚሳኤል ብርጌዷን ልታሰልፍ ትችላለች፤ ሳዉዲ አራቢያ ገንዘቧንና ለጦርነቱ ከነዳጅ ጀምሮ የህክምናና ሌሎችንም ቁሳቁስ፣ በተጨማሪም በዲፕሎማሲዉም ቢሆን ትተባበራለች፤ ግብጽም አባይን ዋስትና ታስከብራለች ኤርትራም ባድሜንና አሰብን ዋስትና ታገኛለች ሳዉዲ አራቢያም የአህባሽን መስፋፋት ታስቆማለች፤

ቸር ይግጠመን

ያረጋል ይማም

yemeru@wau.edu

ዋቢ

1 http://www.bbc.com/news/world-middle-east-42706492

2 Will Nile Water Go To Israel? Part 1 - desip - IGC.org

3 “The Clash of Fundamentalism” crusades, Jihad and Modernity.
Tariq Ali. 2002